MCPS MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
www.montgomeryschoolsmd.org
MARYLAND

Malcolm Baldrige
National Quality Award
2010 Award Recipient

አገስት 2013

የተከበራችሁ የ MCPS ቤተሰቦች፡ -

ባለፉት አራት አመታት አንድ የተሻሻለ ስርአተ ትምህርት -- ስርአ የተሰየመ፣ ከመአለህፃናት ጀምረን፣ አንድ ባንድ ስንዘረጋ ቆይተናል። በሚመጣው የትምህርት አመት፣ ስርአተ ትምህርት 2.0 በሁሉም የ Montgomery County Public Schools (MCPS) የትምህርት ክፍሎች ከመአለህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል ተግባራዊ ይሆናል።

ስርአተ ትምህርት 2.0 በጠንካራ የምርምር አካል የተመሰረተና ይበልጥ የተሟላ ትምህርት እንዲያቀርብ የተተለመ ሲሆን፣ በአካዴሚክስና በህይወት ስኬታማ ለመሆን እጅጉን አስፈላጊ የሆኑት ሂሳዊና የፈጠራ አስተሳሰብ ችሎታዎችንም በተጨማሪ ያዳብራል። በሂሳብ፣ በንባብ፣ እና በፅሁፍ ስርአተ ትምህርት የተመሰረተው በአዲሱ በአለም አቀፍ ደረጃ ግፊት በሚደረግበት በሜሪላሳንድና በሌሎች 45 ስቴቶች ተቀባይነት ባገኘው በ Common Core State Standards ነው። በተጨማሪም፣ ስርአተ ትምህርት 2.0 - ባለፉት 10 አመት ወቅቶች በጥበት ምክንያት ገሸሽ ተደርገው በነበሩ መስኮች - በኪነጥበባት፣ በመረጃ መሰረተ ትምህርት፣ በሳይንስ፣ በማህበራዊ ጥናቶች፣ በጤና ትምህርት፣ እና በአካል ማጠንከርያ ትምህርት ተጨማሪ የትምህርት ትኩረት እንዲደረግባቸው ይፈቅዳል። ስርአተ ትምህርት 2.0 ለተማሪዎቻችን በኤሌሜንታሪ ትም/ቤት ጠንካራ የትምህርት መሰረት ለመስጠት እንደሚያግዝ እና በመካከለኛና በ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ለበለጠ ስኬት እንደሚመራ እናውቃለን።

ከስርአተ ትምህርቱ ጋር ይበልጥ እንዲቀናጅና አንድ ተማሪ ምን እንደሚያውቅና ምን ማድረግ እንደሚችል ለወላጆቻችን ተጨማሪ መረጃ ለመስጠት እንዲያስችል አድርገን የኤሌሜንታሪ ሪፖርት ካርዳችንን አሻሽለናል። "በመመዘኛዎች-የተመሰረተ" ሪፖርት ካርድ ከመአለህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል ተማሪዎች በስርአተ ትምህርቱ ውስጥ በተወሰኑት መስኮች እንዴት በመገስገስ ላይ እንደሚገኙና ከክፍል ደረጃቸው ከሚጠበቅባቸው አንፃር በምን ሁኔታ በማከናወን ላይ እንዳሉ ለወላጆች መረጃ ይሰጣል።

ስርአተ ትምህርት 2.0 በማንኛውም የኤሌሜንታሪ ትም/ቤት የመማርያ ክፍል ማስተማርንና መማርን ለማሻሻል ያግዛል። ስለ ስርአተ ትምህርት 2.0 በትምህርት አመት መጀመርያ ላይ በተጨማሪ ይሰማሉ፣ ሆኖም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይህንን ድረገፃችንን ይጎብኙ፡ - www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/2.0/ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካለዎት፣ የትም/ቤትዎን ርእሰ መምህር ይገናኙ።

ከአክብሮት ጋር

Joshua P. Starr, Ed.D.
Superintendent of Schools